# ከአንድ ባልና ሚስት ከአገር ቤት ሲመለሱ ያገኘሁትን ዜና ላጋራችሁ

ግርማ ወልደማርያም

**13 ማርች 2018**

ከአውስትራሊያ ቤተሰባቸውን ለማየት ከሶስት ልጆቻቸው ጋር አገር ቤት የሄዱትን ባልና ሚስት በስድስት ሳምንታት ቆይታቸው ያጋጠማቸውና ያዩትን ከአሥር ቀናት በፊት ወደ አውስትራሊያ ሲመለሱ ያጫወቱኝን በጣም አጠር አጠር ባሉ ነጥቦች ነጥቤ ላካፍላችሁ። ይህ ትንሽ/ጢቆ ጽሁፍ ካለፉት አራት ሳምንታት ጀምሮ፣ በኢትዮጵያ የነገሰው 'የትግሬዎች ወይስ የሕወሃት የበላይነት ነው' በተሰኘ አርእስት ሲደረግ ለነበረው ክርክር ትንሽ አስተዋጾ ያበረክት ይሆናል።

1. አ/አበባ የሚኖሩ ዘመዶቻቸውን ለመጠየቅ መኪና ያለው አንድ ዘመዳቸው ይዟቸው ሲሄድ ሁለት ትግርኛ ተናጋሪ የትራፊክ ፖሊሶች አስቁመውት ፣ ከ 20-30 ብር በላይ በማያስቀጣ ትንሽ ሥህተት የመኪናውን ታርጋ ነቅለው ይወስዱበትና 3000 ብር ካልከፈል ይሉታል፤ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ ተሳፋሪዮቹ 2000 በር ጉቦ ከፍሏቸው የመኪናው ታርጋ መልሰውለት ጉዞዋቸውን ቀጠሉ ።

2. በእነሱ ምክንያት ዘመድ አዝማድ ተጠርቶና ትልቅ የእራት ግብዣ ተዘጋጅቶ፣ ተጋባዦቹ የምግብ ገበታ ጋ ሲቀርቡ የአካባቢውን መብራት ድርግም ብሎ ይጠፋል ፤ ጋባዡ አባወራ ልምድ ስላለው ፣ ወዲያውም ወደ አካባቢዩ የመብራት ሃይል መሥርያ ቤት ሄዶና ገንዘብ ከፍሎ ለእርሱ ቤት ብቻ መብራት አሥቀጥሎ ይመለሳል። በአዲስ አ/አ ከተማ መብራት ድንገት የሚጠፋው በቴክኒክ ጉድለት ብቻ እንዳልሆነ፣ ነገር ግን ለሁለት አበይት ምክንያቶች ሆን ብለው መብራት እንደሚያጡፉ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ተነግሯቸዋል። ይኸውም:-

ሀ> ከአ/አበባ ከተማ እስኪወጡ ፣ በተላልቅ በእጅና በመኪና ባትሪዮች መብራት እየታገዙ -ሃብት፣ንብረትና ጥሬ ገንዘብ ወደ ትግራይ ለማጓጓዝ

ለ> ከላይ እንደተገለጸው የመብራት አገልግሎት በመቸርቸር ከግለስዎችም ሆነ ከድርጅቶች ሕገውጥ ገንዘብ ለመሰብሰብ። እንደ እነዚህ ህገወጥ ገንዘብ ያለበት ቦታ የሚሰሩት ትግርኛ ታጋሪዮች ብቻ መሆናቸውንም ከአካባቢዩ ነዋሪዮች ተነግሯቸዋል።

3.ተወልዶ ያደጉበትን፣አያቶቻቸውን፣ ቅድመ አያቶቻቸውን፣ቅመአያቶቻቸውን ወዘተ..የኖሩበትን ቄየ/ እርስት በመጤ ትግሬዎች ተቀምተው፣ ለማስመለስ አቤቱታ ሲያቀርቡ ፤ መሬት የመንግሥት ነው አርፋችሁ ተቀመጡ መባላቸው። በቡታዠራ አስተዳደር መሥሪያ ቤት ይሰሩ የነበሩ በጣም ጥቂት ጉራጌዎች ተምሳሳይ ጥያቄ ለሚያነሱ ጉራጌዎች ይሚገቱ ስለነበረ ፤ በሙሉ ከሥራቸው ተባርረው በትግሬዎች የተተኩ መሆናቸውን

4.በቡታዠራ የማዕድን ውሃ(mineral water) ተገኘ መባሉን ሲሰሙ፣በጣም ብዙ ትግሬዎች ወደ ቡታዠራ እየጎረፉ እንደሆነ

5.የቡታዠራ ሁነኛ ንግዶች ፡-ቤንዚን ማደያ፣የእጅ ሥልክ ፣ኤሌክትሮኒክስና ማናቸውም ጥሩ ገቢ የሚያስገኙትን ሸቀጣ ሸቀጦች ብትግሬዎች የተወሰደ መሆኑን፤ ቅም-አያቱን፣ቅድመ-አያቱን፣አያቱን- የዚያ አካባቢ ቡቃያ የሆነውን (indigenous) ማኅበረሰቡ በድኅነት ቅስሙ የተሰበረ መሆኑን፤እነሱ ግን በበልጽግናና በሃብት እየዋኙ የሚኖሩ መሆናቸውን (being submersed in wealth)

6. በዚህ በያዝነው ዓመት የቡታዠራ መድሃኒዓለም ቤተክርስቲያን ምዕምናን የጥምቀት በዓል በሥነ-ሥርዓት እንዳያከብሩ የተደረገባቸው የቦታ እቀባ። የቤተክርስቲያኑ አካባቢ መሬት ለእንቬስተሮች በመሸጡ ፣ታቦት ተሸካሚውና ታቦት አጃቢውን ምዕምናኑ የሚጓዝበትን ቦታ አጥበው ስላጠሩባቸው መፈናፈኛ አጥተው እንደነበረ። ‘ሆድ ያባው ብቅል ያወጣዋል’ እንደሚባለው-የመብት ረገጣውን፣የፍትኅ እጦቱን፣የሥራ እጦቱን፣ የኑሮ ጉስቁልናውን ወዘተ..ብሶቶች ተጨምሮበት ምዕምናኑ ፡- ዱላ፣ ቆጨራ፣ ቢላዋ፣ሰንጤ፣ ሞቋሚያ፣መስቀል ወዘተ..ይዘው ውጥተው ከወያኔ ፖሊሶችና ካድሬዎች ጋር ተፋልመው ፤ አጥሩን አፍርሰውና ቦታውን አስፍተው የጥመቀት በአላቸውን አከበሩ።

አው ሕዝብ ሁሌም አሸናፊ ነው!

የሕዝብ ሃይል!የሕዝብ ቁጣ የሚበግረው ነገር የለም !!

“የሹሮ ድንፋታ እንጀራ እስኪመጣ ነው” ይባል የለም፤ የወያኔዎችም ድንፋታ ገናናውና ጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብሎ እኪወጣ ነው።